**<u>ወልቃይት ላለፉት ሺህ ዓመታት በትግራይ ስር ተዳድራ አታውቅም</u>**

**<u>የ700 ዓመት የታሪክ ሰነዶች ማስረጃዎች</u>**

**( Ze Addis )**

በህ.ወ.ሀ.ት የሚዘወረው የኢትዮጵያ መንግስት (ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ) አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ከወሰዳቸው ዓብይ ኩነታት አንዱ ፣ የሀገሪቱን የፖለቲካን የአስተዳደር ካርታን መቀየሩ እንደሆነ ይታወቃል።

የጥንቱ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ካርታ በ1994 ዓ.ም ቢቀየርም ፣ አዲሱ ካርታ ብዙ የማንነት ጥያቄዎችንና እሮሮዎችን አስነስቷል። ይህ የማንነት መጨፍለቅና የዳግም መካለል ጥያቄ ከሚነሳባቸው ቦታዎች ውስጥ ከጎንደር ተቆርሶ ወደ ትግራይ የተካለለው የወልቃይት ጸገዴና አላማጣ -ዋጃ ሕዝብ አንዱ ነው።

የወልቃይት - ጠገዴም ሆነ የአላማጣ -ዋጃ ሕዝብ ላለፉት 21 ዓመታት ያለማቋረጥ ወደ ትግራይ መካለላቸውን በመቃወም አቤቱታ ሲያሰሙ ከርመዋል። ጥያቄውን ለማስቆምና ለመጨፍለቅ ብርቱና ዘግናኝ እርምጃዎች በህ.ወ.ሀ.ት መራሹ መንግስት ቢካሄድም ፤ እምቢታው እስካሁን አልቆመም። ይልቁንም የማንነት ጥያቄው እየተጋጋለ መጥቷል። በተለይ ላለፉት ስድስት ዓመታት በርካታ ጠንካራ እንቅስቃሴዎች እየታዩ ነው። ይህንን የሚያስተባብሩት የሕዝቡ ተወካይ ኮሚቴዎችም የሃምሳ ሺህ ሰው ፊርማ በማሰባሰብ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በመድረስ ሰላማዊ ጥያቄያቸውን እያሰሙ ነው።

ይህንንም ወቅታዊ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ፣ ሀገር ውስጥ ያሉና በውጭ ሀገር ያሉ በርካታ ሚድያዎች በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ዘገባዎችን ና አስተያየቶችን እያስተናገዱ ነው ። ለዛሬውም ጽሁፌ መነሻ የሆነኝ ፣ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ የትግርኛው ዘርፍ የወልቃይት ጠገዴን የማንነት ጥያቄ በተመለከተ ከዶክተር ገላውዴዎስ ዓርአያ ጋር ያደረገው ቃለ መጠይቅ ነው። ጥያቄና መልሱ ይሄንን ይመስል ነበር።

ጋዜጠኛው አቶ በትረ ለዶክተር ገላውዴዎስ [1]

> *"ወልቃይት ከጥንቱም ጀምሮ የትግራይ አካል ሆኖ ኢያውቅም የሚሉ ወገኖች አሉ። ስለዚህ አተያይ ምን ይላሉ"*

ብሎ ለጠየቃቸው ጥያቄ ዶክተር ገላውዴውስ ሲመልሱ

> *"ወልቃይት ከጥንት ጀምሮ በትግራይ ስር አልነበረችም የሚለው አባባል የታሪክ መሰረት የለውም ፣ ጌጋይ እዩ ( ስህተት ነው)።"*

---

[1] http://tigrigna.voanews.com/a/welkite-tsegedie-historical-perspective-by-dr-geladewos-araya-part-1-and-2/3253236.html

በማለት ከመለሱ በኋላ እንዲህ አይነት የማንነት ጥያቄ ሲነሳ ጥያቄው መመለስ ያለበት የታሪክ ሰነድን በመመርመር መሆን እንዳለበት ገልጸዋል።

ዶክተሩ እንደተናገሩት የወልቃይት ጠገዴ መሰል የማንነት ጥያቄ በሚነሳባቸው ቦታዎች ላይ መፍትሔ መስጠት የሚቻለው ያለፈ ታሪክን በመመርመርና ይዞታው የማን መሆኑን ፣ማን ይኖርበት እንደነበረ ፣ በመለየት ነው። ይህ ሁሉን የዓለም ምሁራን የሚያስማማ ሳይንሳዊ እሳቤ በመሆኑ በዚህ ላይ ጥያቄ የለኝም። ከዶክተር ገላውዴዎስ ጋር የማልስማማበት ጉዳይ :-
" ወልቃይት ድሮ( በተለይ በኣጼ ዮሓንስ ዘመን ወይም በጥንት ታሪኳ) በትግራይ ስር ነበረች" የሚለውን መሰረት የሌለው አስተያየት ነው። ወልቃይት ጠገዴ በታሪኳ በትግራይ ስር ሆና አታውቅም። ሁላችንንም የሚያስማማን የታሪክ ሰነድ መረጃ ነውና ታሪክን እንመርምር። በዚህ ጉዳይ ብዙ ግዜ የሚነሱት አጼ ዮሓንስ ስለሆኑ ከሳቸው ዘመን ልጀምር

1. <u>ወልቃይት ጠገዴና አላማጣ ኮረም በአጼ ዮሓንስ ዘመን በትግራይ ሥር አልነበሩም</u>
   <u>የታሪክ ሰነድ ማስረጃ</u>


አጼ ዮሓንስ ከ 1871 ዓ.ም እስከ 1889ዓ.ም ( እ.ኤ.አ) ኢትዮጵያን የመሩ ንጉስ ናቸው። ንጉሰ በንግሥና ዘመናቸው የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ቢኖራቸውም ፣ ከጠላት ደርቡሽ ጋር በመፋለም ለሀገራቸው ሕይወታቸውን የሰጡ ሰው ናቸው። ብዙ የሕወሀት አፈ ቀላጤዎች ፣ ከወልቃይትና ጠገዴ ጋር በተያያዘም የሚጠቅሱት እሳቸውን ነው::

*" ወልቃይት እና ጠገዴ ፣ ጥንት በአጼ ዮሓንስ ዘመነ መንስግት በትግራይ ስር ነበረች "* በማለት እንደ ዋና መከራከርያ ሲያቀርቡት ይደመጣል:: እውነታውን የዘገቡት የታሪክ ሰነዶች ናቸውና የታሪክ ሰነዶችን እንመርምር።በአጼ ዮሓንስ ዘመን የነበረው የትግራይ ግዛትና ፣ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ግዛት ምን እንደሚመስል በዝርዝር በሀገር ውስጥና በውጭ ሊቃውንት ተጽፏል። አንዱም ግን ወልቃይት -ጠገዴ ወይም አላማጣ ዋጃ በትግራይ ስር ነበሩ አይልም። ለዚህም የእውቁን የፈረንሳዊ የጂኦግራፊ ፕሮፌሰር ኤሊስ ሬክለስ መጽሓፍን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል።

በዩንቨርሲቲ ኦፍ ብረስልስ የኮምፓራቲቭ ጂኦግራፊ (University of Brussels, Professor of Comparative Geography) ፕሮፌሰርና የዴፓርትመንቱ ሀላፊ የነበረው ይሄው ፕሮፌሰር ፤ በ1880 ጀምሮ በርካታ መጽሓፎችን በዓለም ጂኦግራፊ ላይ ጽፏል። እነዚህም መጽሓፍቱ ከለንደንና ፓሪስ ጆኦግራፊካል ሶሳይቲ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ አድርገውታል።

ከነዚህ መጻሕፍት አንዱ በ 1880የተጻፈው The Earth and its Inhabitants [2]የሚለው ሲሆን፤ ዘጠን ተከታታይ ክፍሎች አሉት። የዚሁ መጽሓፍ ክፍል አራት የሰሜን እና ምስራቅ አፍሪካን የወቅቱን ጂኦግራፊ በዝርዝር ይተነትናል:: በአጼ ዮሓንስ ዘመን የነበረውንም የኢትዮጵያን ክፍላተ ሀገራት በዝርዝር ቁልጭ አድርጎ እንዲህ ጽፎታል:: [3]

"The Amhara government provinces are : Dembia, Chelga, Yantangera, Dagossa, Kuarra, Begemidir, Guna, Saint, Wadla, Delanta, Woggera, Simen, **Tselemt,** Armachiho,**Tsegede**, Kolla Wogerra **Waldiba and Wolkait"**


Exit The Earth and Its Inhabitants ...: North-east Africa – Elisée Reclus

ADMINISTRATIVE DIVISIONS OF ABYSSINIA.

| Governments. | Provinces. | Fluvial Basins. | Climatic Zones. | Towns. |
|---|---|---|---|---|
| | Dembea | Blue Nile | Dega, Voïna-dega | Gondar |
| | Chelga | ,, Atbara | ,, | Chelga |
| AMHARA | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] |
| | Woggara | Takkazeh, Atbara | Voïna-dega, Dega | —— |
| | Simen | ,, | Dega | Inchatkab |
| | Tselemt | ,, | Voïna-dega, Kwalla | —— |
| | Ermecho | Atbara | Kwalla | —— |
| | Tsagadeh | ,, | ,, | —— |
| | Kolla Wogara | ,, | ,, | —— |
| | Waldebba | Takkazeh | ,, | —— |
| | Wolkaït | ,, | ,, | Nagada |
| | Achefer | Blue Nile | Voïna-dega | Isinala |
| | Macha | ,, | Dega, Voïna-dega | —— |
| GOJAM | Gojam | ,, | ,, ,, | Monkorer |

443 / 495

ይህን ሊንክ ቢጫኑ መጽሓፉን ያገኙታል:: በገጽ 443 ላይ ከዚህ በታች ያሰፈርኩትን ሙሉ CTR + Click ቢጫኑ በአጼ ዮሓንስ ዘመን የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ዝርዝር ምን እንደሚመስል ያገኙታል)
(https://play.google.com/books/reader?id=Y4WbCSAU7kQC&printsec=frontcover&output=reader&hl=en&pg=GBS.PA448)

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ይህ ጽሁፍ የተጻፈው በ1880ዎቹ አጼ ዮሃንስ የሀገሪቱ ንጉስ በነበሩበት ዘመንና የተጻፈውም በግዜው ከነበሩ ከተለያዩ የጂኦግራፊካል ሶሳይቲዎች የወርቅ ሜዳይ ተሸላሚ በሆነ ባለሙያ ፕሮፌሰር ነው::ይህ በ1880ዎቹ የተጻፈው መጽሓፍ እንደሚያስረዳው በአጼ ዮሓንስ ዘመን ወልቃይት: ጠለምት : ዋልድባ : አላማጣ : በሙሉ በትግራይ ስር አልነበሩም:: እነዚህን ቦታዎች በስም ጠቅሶ እንደሚነግረን በትግራይ ስር ሳይሆን በጎንደር ስር ነበሩ::

---

[2] The Earth and Its Inhabitants, Africa: South and east Africa
by Elisée Reclus 1890

" በአጼ ዮሓንስ ዘመን ወልቃይትና ጠግዴ በትግራይ ስር ስለነበሩ ነው አሁን ወደ ትግራይ የጠቀለልናቸው " የሚለውን የወያኔ ፈጠራ መሰረተ የሌለው መሆኑን ይሄ መረጃ ያሳየናል::

ከአጼ ዮሓንስ በፊትስ እነዚህ ቦታዎች ይተዳደሩ የነበሩት በማን ነው? የሚለውን እንመልከት። ወደ አጼ ቴዎድሮስ ዘመን እንጓዝ

## 2. በኣጼ ቴዎድሮስም ዘመን ወልቃይትጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም የታሪክ ማስረጃ ሰነዶች

በኣጼ ቴዎድሮስ ( 1818 – 1868 እ.ኤ.ኣ) የነበሩ ስመ ገናና ኢትዮጵያዊ ንጉስ ነበሩ:: በየቦታው የነበሩ መሳፍንትን አሸንፈው ፣ ማዕላዊ መንግስት ከመሰረቱ በኋላ ፣ ቀጣይ ራዕያቸው የምዕራብያውያንን ቴክኖሎጂ እዚሁ ኢትዮጵያ እንዲመረት ማድረግ ነበር:: ለዚህም ከበርካታ አውሮፓ ሀገራት ጋር ግንኙነት መስርተው ነበር:: የአውሮፓውያን ጥበበኞችን ኢትዮጵያ ለማስቀረት እና ጥብቅ ግንኑነት ለመመስረት ፣ አጼ ቴዎድሮስ ልጃቸውን ለአንድ ስዊስ ኢንጂነር እስከመዳር ደርሰው ነበር:: በዚህም ምክንያት በርካታ አውሮፓውያን ጠቢባን በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን ኢትዮጵያ መጥተዋል:: እነዚህም ባለሙያዎች ኢትዮጵያ መጥተው ስለ ሀገሪቱ በዝርዝር ጽፈዋአል:: የእንግሊዝ መንግስትና የኢትዮጵያ ግንኑነት መሻከር ሲጀምር ፣ እንግሊዞች ስለኢትዮጵያ ይበልጥ የማወቅ ፍላጎታቸው ጨመረ::

የእንግሊዝ መንግስት የ intelligence ሰዎችም የእንግሊዝ መንግስት ፓርላማና የጸጥታው ኃይል ኢትዮጵያን በሚገባ ያውቃት ዘንድ ትዕዛዝ ወጣ:: የእንግሊዙ Topographical and Statistical Department of The War Office ኤ . ሲ ኩክ ( A. C. Cook) በተባለ እንግሊዛዊ ኮሎነል አማኻኝነት ስለ ኢትዮጵያ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በተለያዩ እውሮፓውያን ተጻፉ መጻሕፍት ባንድ ላይ እንዲጠርዘ ተደረገ:: የሚደንቀው ይሄ መጽሓፍ በ 1867 ዓ.ም እ.ኤ.ኣ የታተመው በግስቲቷ ጥያቄ ለእንግሊዝ ሀውስ ኦፍ ኮመን ሎወር ሀውስ ግባአት ( House of Common lower House) ይውል ዘንድ መሆኑ ነው:: በዚሁ መስሓፍ ውስጥ ፤ የወቅቱ የኢትዮጵያ ዝርዝር ጉዳይ ተጽፏል:: ይሄውም መጽሓፍ ስለ ወልቃይትና ጠግዴም በኣጼ ቴዎድሮስም ይሁን ከሳቸው በፊት በማን ስር ይተዳደሩ እንደነበር በዝርዝር ያትታል:: [4]

> "The Provinces of Amhara are : Simen, Waldibba, Wolkait,Wogera,Chilga, Kuara, Belesa, Fogerra, Damot, Gojjam, Begemidir, Beshilo ….. Waldiba situated to the NW of Semein between the Tekeze and the Angereb, extends as far as the junction of the two rivers. Welkait is to the west Of Waldiba it is intersected through its whole length by the two river tekuar and guang. It is more wooded than waldiba.."
>
> Routes in Abyssinia (printed in 1867 G.C) page 188

[4] Routes in Abyssinia (printed in 1867 G.C) page 188

https://archive.org/stream/routesinabyssini00cookrich#page/186/mode/2up/search/1

(ይህን ሊንክ በመጫን ሙሉ መጽሐፉን ማውረድ ይቻላል)

ይሄው ታሪካዊ መጽሓፍ በወቅቱ የነበረውንም የትግራይ ክፍለሀገር ድንበር እና ግዛት እነማን እንደነበሩ በማያሻማ ቋንቋ እንዲህ ይነግረናል Routes in Abyssinia (printed in 1867 G.C) page 188

> “The territory of Tigre whose capital is Adwa, is bounded on the West by Shire, on the Southwest by Temben and Adet on the South by Geralta on the South –East by Haramat, on the East by Agame, and on the North by the rivers of Mereb and Belessa”[5]

የትግራይ ግዛትስ? ብሎ ለሚጠይቅ ወገን ፤ ይሄው መጽሓፍ በወቅቱ የነበርቸው ትግራይ ምን እንደምትመስል እንዲህ ሲል አስፍሮታል በዚሁ መጽሓፍ ላይ ገጽ 187 - 188 የትግራይን ግዛት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል

> "The territory of Tigray whose capital is Adwa is bounded on the west by Shire, on the south west by Temben and Adet, on the south by Geralta, on the South East by Haramat,on the East by Agamae, and on the North by the Rivers Mereb and Belessa" Routes In Abyssinia page 187

https://archive.org/stream/routesinabyssini00cookrich#page/186/mode/2up/search/1

(ይህን ሊንክ በመጫን ሙሉ መጽሐፉን ማውረድ ይቻላል)



እዚህ ላይ በ 18ተኛው ክፍለ ዘመን የትግራይን ወሰኖች በማያሻማ ሁኔታ በግልጽ አስቀምጦታል። የትግራይ ወሰን በምዕራብ - ሽሬ ፤ በምዕራብ ደቡብ - ተምቤን እና አዴት ፤ በደቡብ - ገር አልታ ፤ በምስራቅ - ኢጋሜ ፤በሰሜን - መረብና በለሳ ናቸው። የታሪክ ሰነዶች በአጼ ቴዎድሮስም ዘመን እንደሚነግረን ፤ ወልቃይትና ጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም።

ከዛስ በፊት ፤ ወልቃይትና ጠግዴ በትግራይ ስር ነበሩን? አሁንም የታሪክ ሰነድ እንመርምር።

## 3. በዘመነ መሳፍንት ዘመንም ወልቃይትጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም የታሪክ ማስረጃ ሰነዶች

እንደሚታወቀው ከአጼ ኢዮአስ ሞት ጀምሮ ፤ አጼ ቴዎድሮስ እስኪነሱ የነበረው ዘመን ዘመነ መሳፍንት ይባላል:: በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት አልነበራትም:: መሳፍንቶች የገነኑበትና በሀገሪቱ ማዕከላዊ አስተዳደር የጠፋበት ዘመን ነበር:: በዚህ ማዕከላዊ የመንግስት ሕግ በሌለበት ወቅት እንኳን ወልቃይት፥ጠገዴ፥ ዋልድባ ፥ አላማጣ፥ ኮረም እና የመሳሰሉ ቦታዎች በትግራይ ስር አልነበሩም:: አሁንም ማስረጃ እነሆ!

ጀምስ ብሩስ የተባለው ስኮትላንዳዊ ፥ በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ መጥቶ ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ምን ትመስል እንደበረ ፥ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል:: እያንዳንዱ መስፍን ግዛቱ የት ድረስ እንደነበረ፥ የትኛው መስፍን ማንን ይገዛ እንደነበረ በሰፊው ተንትኖታል:: በዚህም መሰረት ስለ ትግራይ ግዛትና እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ይሰጣል ::
Travel to discover source of the Nile Volume 3 page 582

> “Tigre is bounded by the territory of the Bahirenegash that is by the river Mereb on the East and Taccazze upon the west. It is about one hundred and twenty miles broad from E. to W. and two hundred from N. to S. “

ጀምስ ብሩስ በዚሁ መጽሓፉ Chapter 10 ላይ Geographical division of Abyssinia into province በሚለው አንቀጹ ላይ በይበልጥ ቁልጭ አድርጎ እንዲህ ያስቀምጠዋል

> The first division is called Tigre, between Red Sea and the river Tekeze. Between that River (Tekeze) and the Nile Westwards where it bounds the Oromo, it is called Amhara.
> ካለ በኋላ ወረድ ብሎ ይበልጥ ጉዳዩን ሲያስረዳ
> "Tekezze is the natural boundary between Tigre and Amhara"

ከላይ ለአብነት ያስቀመጥኳቸው ሊቃውንት በግዜ፣ በቦታና በዜግነት አይገናኙም። ለምሳሌ በአጼ ዮሓንስ ዘመን የነበረው አሊስ ሬክለስ ፈረንሳዊ ( French) ነው። በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረውን የኢትዮጵያ ግዛት የጻፈው ደግሞ እንግሊዛዊ ነው ( British) ። ጀምስ ብሩስ ደግሞ ስኮትሽ ( Scottish)ነው። ግን ሁሉም በተለያየ ግዜ መጥተው ያዩትና የተገነዘቡትን ጽፈዋል። የሚናገሩት አንድ ና ተመሳሳይ ነው። እውነት ምን ግዜም አንድ ናትና!

### 4. ወልቃይት በ1630ዎቹስ በማን ስር ነበረች? እውን ዶክተር ገላውዴዎስ የነገሩን እውነት ይሆን?

አሁን ዶክተር ገላውዴዎስ ዓርአያ ስለ ወልቃት ጠገዴ ተጠይቀው ሲመልሱ : ጥንት ወልቃይት በትግራይ ስር ስለመሆኗ እንደማረጃ ያቀረቡትን መጽሓፍ እንመልከት። ይሄ መጽሓፍ የተጻፈው በ1634 ሲሆን ጸሓፊውም ኢማኑኤል በሬዳ ይባላል። በወቅቱ የነበረውን የትግራይ ግዛት በዝርዝር አስቀምጧል። እሱም እንደሌሎቹ ጸሓፍት የትግራይ ድንበር ተከዜ እንጂ ተከዜን ተሻግረው ያሉት ወልቃይትና ጠግዴ ናቸው አይልም። እንዴት አንድ ፒኤችዲ የያዘ ሰው ይሄን ያህል የወረደ ውሸት ይዋሻል? ፍርዱን ለአንባቢ እሰጣለሁ። የእሳቸው ቃለመጠይቅ ይህን ሊንክ ከዚህ ጽሁፍ መጨረሻ ዋቤ መጻህፍት ላይ አለ:; ቢጫኑ ያገኙታል። የጠቀሱት መጽሓፍም የሚለውም እነሆ

«Tractatus tres historico-geographici (1634): A seventeenth century historical and geographical account of Tigray, Ethiopia (Aethiopistische Forschungen) 1634» መጽሀፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ስለ ትግራይ ግዛት እንዲህ ይላል፡


> <<Among all the kingdoms that the Emperor of Ethiopia possesses today one of the greatest if not the greatest and the most important is the kingdom Tigre. From north to south, that is from the limits of the Hamasen to Enderta, it covers an areas of from ninety to one hundred leagues (3.2 miles); and from the east, which is besides Dancali, located at the entrance to the Red sea to the southern end of the Red Sea, to the west bounded by the Tekezze River beside the Semen, it covers an area of similar size, so that the Kingdom has a nearly circular shape. >>

ዶክተር ገላውዴዎስ ከየት አምጥተው "ይሄ መጽሓፍ ይሆን ወልቃይትና ጸገዴ በጥንት ግዜ የትግራይ ነበሩ ይላል" ያሉት? አንባቢ ይፍረድ

አሁንም ወደኋላ እየራቅን እንሂድና ወልቃይት ጠገዴ በነ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በማን ስር ነበርች? የሚለውን እንመልከት

## 5. በኣጼ ዘርዓ ያዕቆብ ( 14ኛው ክፍለ ዘመን) ዘመንም ወልቃይትጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም የታሪክ ማስረጃ ሰነዶች

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በኢትዮጵያ ታሪክ ከተነሱ ሃያልና ሊቅ ነገስታት ውስጥ አንዱ ነበሩ:: በቀድሞ ስሙ ፈጠጋር በአሁን ስሙ ኦሮሚያ አዋሽ ወንዝ አካባቢ የተወለዱት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ፥ የሓድያ ሲዳሞ ንጉስ ልጅ የሆነችውን እሌኒን አግብተው ፥ በ 37 ዓመታቸው ከነገሱ ጀምሮ በርካታ ዓበይት ስራዎችን አከናውነው አልፈዋል:: እኒሁ ንጉስ ከፍተኛ የጥበብ ፍቅር የነበራቸውና ከመሆናቸው ባሻገር ፥ ራሳቸው ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል:: በሳቸው ዘመንም ብዙ መጻሕፍት እንዲጻፉ ድጋፍ በመስጠታቸው አያሌ መጻሕፍት በሳቸው ዘመን ተጽፈዋል:: ከነዚህ መጻሓፍት አንዱ በአክሱም ንቡረ ዕድ የተጻፈው ዜና አክሱም መጽሃፍ አንዱ ነው:: ዜና አክሱም ከሃይማኖያትዊ ሐተታው ባለፈ ስለ 14ኛዋ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በዝርዝር ጽፎታል:: ይህ መጽሓፍ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ወሰንና ታሪክ ብቻ ሳይሆን የክፍላተ ሀገራቱንም ድንበር ጥንቅቅ አድርጎ ዘግቦታል:: የትግራይንም ክልል በካርታና በጽሁፍ ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጸዋል ::[6]




6 Ethiopia: the Land, Its People, History and Culture
By Yohannes Mekonnen

ይህም መጽሓፍ በተመሳሳይ መልኩ የሚነግረን፣ ወልቃይትና ጠገዴ በፍጹም ፣ የትግራይ አካል አንዳልነበሩ ነው።
ዮሓንስ መኮንን Ethiopia : the land, its people , History and Culture በሚለው መጽሓፉ Page 351 በአጼ ዘርዓ ያ ዕቆብ ዘመነ መንግስት የነበረውንና በመጽሓፍ አክሱም የተተነተውን የትግራይን ካርታ እንዲህ ያቀርበዋል

> “The Book of Axum.. Shows a traditional schematic map of Tigray with its city Axum at its center surrounded by the thirteen principal provinces: Tembein, Shire, Seraye, Hamasen, Bur, Sama, Agame, Amba Senait, Geralta, enderta, Sahart and Abergele” [7]

"

በተመሳሳይ ሁኔታም The World through Maps: A History of Cartography (ገጽ 352 ይመልከቱ)
By John R. Short የተጻፈው የዓለም ጂኦግራፊን የሚተርከው መጽሓፍ በ15ኛው ክፍለዘመን የነበሩ የትግራይ ግዛቶች ከላይ የተጠቀሱት መሆናቸውን መጽሓፈ አክሱምን በመጥቀስ ያስረዳል።ይህም መጽሓፍ በተመሳሳይ መልኩ የሚነግረን፣ ወልቃይትና ጠገዴ በፍጹም ፣ የትግራይ አካል አንዳልነበሩ ነው።

## 6. <u>ቋንቋን መሰረት ወዳደረገ ክለላን አንመልከት</u>


የኢትዮጵያውያን ወጣቶችና አርበኞች ቁጣ ያሳሰበው ጣልያን፣ ኢትዮጵያን በቋንቋና በዘር በትኖ ለመግዛት ያቀደውን መርዝ ይፋ አወጣ። የዚህ እቅድ ፊታውራሪ ከሆኑት አንዱ ፋሺስቱ Baron Roman Prochàzka አቢሲንያ ዘ ፓውደር ባረል( Abyssinia : the Powder barrel) በሚል መጽሓፉ ላይ እንዳስቀመጠው፣ ኢትዮጵያውያንን ለመግዛት በዘር መከፋፈልና በመሀከላቸውም ጥላቻን በመዝራት እርስ በርስ ለማናከስ፣ ሀገራቸውን በዘር መከለል የሚለውን እቅድ መተግበር ጀመረ። በዚሁም መሰረት ፣ ዘርንና ቋንቋን መሰረት ባደረገ ሽንሽና ኢትዮጵያን አምስት ቦታ ከፈላት።

እነዚሁም ክልሎች አማራ: ኤርትራ(ትግሬ); ሐረር: ኦሮሞ-ሲዳማ : ሸዋና ሶማሌ ናቸው። ጣልያን ይሄንን የግዛት ሽንሽና ሲያካሂድ መሰረት ያደርገው ዘርና ቋንቋን ነበር። የሚከተለውም ሰማንያ በሃያ የሚለውን መርህ ነበር። ከሰማንያ በመቶ በላይ ሕዝቡ የሚናገረውን ቋንቋ መሰረት በማድረግ ወደየ ክልሉ ይደለደላል። ሸዋን ግን ለብቻው ለይቶ መቆጣጠር ይገባል ብሎ በማመኑ ሸዋን ና ሀረርን  ለብቻ ለይቶታል። ወደ ነጥባችን ስንመጣ በዚህ የቋንቋ ሽንሽና መሰረት ወልቃትና ጠግዴና ጠለምት ወደ ትግራይና ኤርትራ አልተካተቱም። በጎንደር ስር ነበሩ።

እዚህ የጣልያን ቋንቋን ና ዘርን መሰረት ያደረገ ካርታ ላይ በግልጽ እንደሚታየው ፣ የትግራይ ድንበት ተከዜ እንጂ - ከተከዜ ተሻግሮ አይደለም። ላልፉት 25 ዓመታት ተቃዎሞ ሲካሄድባቸው የከረሙት ወልቃይት - ጠገዴ - አላማጣ ኮረም በፍጹም በትግራይ ስር እንዳልነበሩ በግልጽ ያሳየናል።

---

[7] ክፍል አንድ መጽሓፈ አክሱምን እዚህ ሊንክ ላይ ያገኙታል
https://archive.org/details/liberaxumae00pari





http://www.igmi.org/ancient/immagine.php?cod=14557

እንደ ትግራይ ኦን ላየን የመሳሰሉ የህወሀት ልሳኖች ደጋግሞ በማውራት ሊያሳምኑ የሚፈልጉት ውሸት አለ:: ይሄውም ወልቃይት ጸገዴና ሌሎች ወደ ትግራይ የተካለሉ ቦታዎች ጥንት የትግራይ እንደነበሩና አጼ ኃይለ ሥላሴ የምስራቃዊ ትግራይ ገዥ ከነበሩት ከደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሳ አርዓያ ጋር በመጣላታቸው - ወልቃይትና

ጠገዴንወደ ጎንደር ወሰዱት የሚል ነው:: ሌላው ውሸት ደግሞ - የቀዳማይ ወያኔን አመጽ ምክንያት በማድረግ ትግራይን ለመቅጣት - ወልቃይትንና ጠገዴን ወደ ጎንደር ከለሉት የሚል ነው::[8]

እስካሁን ከላይ የገለጽኳቸው ሰነዶች ለዚህ ውሸት በቂ ማምከኛ ቢሆኑም : ካርታን መሰረት ያደረገ መረጃ ለሚጠይቅ ሰው -እነሆ:: ይህ ካርታ በጣልያኖች በ1928 ዓ.ም የተሰራ ነው:: ኢትዮጵያን በደምብ ካጠኑ በኋላ ለያንዳንዱ ክፍለሀግር ካርታ ሰርተዋል:: ያኔ ገና ኃይለሥላሴ ጉግሳ አልከዳም:: ያኔ የቀዳማይ እንቅስቃሴ አልነበረም:: የቀዳማይ እንቅስቃሴ በ1943 ነበር:; ይህ ካርታ ግን ከዛ ብዙ ዓመታት በፊት የተሰራ ነው:: አንባቢው አይቶ ይፍረድ




ወልቃይት ጠገዴን ነጥለን ስንመለት ደግሞ ካርታው ይሄንን ይመስላል።

8 https://en.wikipedia.org/wiki/Woyane_rebellion

**በዘመነ መንግስቱ ኃይለማርያም ወልቃይትና ጠገዴ**

በካምብሪጅ ዩንቨርሲቲ በአፍሪካ ጉዳዮች ላይ ይበልጡንም በኢትዮጵያ ታሪክና ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ምርምር ካደሩት ሰዎች ውስጥ በዋነኝነት የሚጠቀሱት ፕሮፌሰር ክሪስቶፈር ክላፓም : እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር 1990 ( ህወሀት አዲስ አበባብ ከመያዙ አንድ አመት በፊት) ድንቅ የሆነ መጽሓፍ አሳትመው ነበር። በዚሁ መጽሓፋቸው ላይም ስለ ወልቃይትና ጠግዴ እንዲህ ሲሉ ይተርኩታል

Christopher Clapham: Transformation and continuity in revolutionary Ethiopia (Cambridge: Cambridge university press 1988 pp 259

> "the area concerned ( welkait -Tsegede) separated from Tigray by impressive natural barrier of Setit Tekezze river has never been governed as part of Tigray at any period in the past, but has come under Gonder and Semein.

<u>ስናጠቃልለው</u>

1. 1420ዎቹ እንደተጻፈ የሚታመነው መጽሓፈ አክሱም በግልጽ እንደሚያሰረዳን የትግራይ ግዛቶችና ወሰኖች 13 ነበሩ። እነርሱም Tembein, Shire, Seraye, Hamasen, Bur, Sama, Agame, Amba Senait, Geralta, enderta, Sahart and Abergele ናቸው።

    ማስረጃ : መጽሓፈ አክሱም , Ethiopia: the Land, Its People, History and Culture By Yohannes Mekonnen

    The World through Maps: A History of Cartography (ገጽ 352 ይመልከቱ) By John R. Short

2. 1634 ዓ.ም የተጻፈው የ እማኑኤል በሬዳ መጽሓፍ Tractatus tres historico-geographici (1634): A seventeenth century historical and geographical account of Tigray, Ethiopia (Aethiopistische Forschungen) 1634» እንደሚያስረዳው የትግራይ ወሰን ተከዜ እንጂ ተከዜን ተሻግረው ያሉት ወልቃይትና ጠገዴ አይደሉም

3.በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያን ጎብኝቶ የነበረው የጀምስ ብሩስ መጽሓፍም በግልጽ የሚናገረው የትግራይ ወሰን ተከዜ እንጂተከዜን ተሻግረው ያሉት ወልቃይትና ጠገዴ አይደሉም

    Travel to discover source of the Nile Volume 3 page 582

4. በአጼ ዮሓንስ ዘመንም የታሪክ ማስረጃዎች የሚያስረግጡት ያንኑ ነው። የትግራይ ደንበር ተከዜ ነው።; ወልቃይትና ጠገዴ በጎንደር ስር እንደነበሩ በግልጽ ፈረንሳዊው ፕሮፌሰረ ሬክለስ ጽፎታል

https://archive.org/stream/routesinabyssini00cookrich#page/186/mode/2up/search/1

5. በአጼ ቴዎድሮስ ዘመንም ወልቃይትም ይህን ጠግዴ በትግራይ ስር አልነበሩም፡;

(https://play.google.com/books/reader?id=Y4WbCSAU7kQC&printsec=frontcover&output=reader&hl=en&pg=GBS.PA448)

6. በጣልያን ግዜም የትግራይ ወሰን በደቡብ እንዳምሆኒ, በደቡብ ምስራቅ አበርገሌ ;በም ዕራብ ሽሬና አዲያቦ ነበሩ እንጂ ወልቃይት ጠግዴ ዋጃ ኮረም እና መሰል ቦታዎች በትግራይ ስር አልነበሩም

7. ወልቃይትንና ጠገዴን ወደ ትግራይ የከለሉት አጼ ኃይለሥላሴ ናቸው፡; ይህም በ1943 ዓ.ም የተካሄደውን የቀዳማይ ወያኔን አብዮት ለመበቀልና ሕዝቡንም ለመቅጣት ነው የሚለው ተረት ተትም መሰረት እንደሌለው እነሆ ይህ ማስረጃ፡፡ ጣልያን ይሄን ካርታ የሰራው በ1928 ዓ.ም ነበር፡፡ ያኔም በአጼው ግዜም የትግራይ ወሰን ያው ነበር

http://www.igmi.org/ancient/immagine.php?cod=14557

8. የህዝብ ቁጥርና በሚነገሩት ቋንቋ ነው ወልቃይትንና ጠግዴን ወደ ትግራይ የከለልነው ለሚለውም - የዘርና የቋንቋ ክልልን ለመጀመርያ ግዜ ኢትዮጵያ ላይ የመሰረተው ጣልያን ነው፡፡ ጣልያን ይህን ካርታ ሲሰራ የራሱን የዘርና የቋንቋ ጥናት አድርጎ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ወልቃይትና ጠግዴን ወደ ትግራይ ሳይሆን ያካለላቸው ወደ ጎንደር ነበር፡፡ ይሄ ከሆነ አንድ ትውልድ እንኳን አላለፈው፡፡ ታድያ ያኔ አብላጫ የነበረው ቋንቋና ሕዝብ አሁን ወዴት ገባ?

9. በዚህ ዘመን ያሉ እውቅ የኢይዮጵያ ነክ ፕሮፌሰሮችም ምስክርነታቸው ያው ነው፡፡የካምብሪጅ ዩኒቨርስቲው ክሪስቶፈር ክላፐማን እንዳጠቃለሉት

"the area concerned ( welkait -Tsegede) separated from Tigray by impressive natural barrier of Setit Tekezze river has never been governed as part of Tigray at any period in the past, but has come under Gonder and Semein.

10. የአጼ ዮሓንስ የልጅ ልጅ ል ዑል ራስ መንገሻ ስዩምም እንዳረጋገጡት " የትግራይ ወሰን ተከዜ እንጂ ተከዜን ተሻግረው ያሉት ወልቃይትና ጠግዴ አይደሉም"

https://www.youtube.com/watch?v=YNVxvuMR9H8

አሁንም ቢሆን የወልቃይት የማንነት ጠያቂዎች የ ሃምሳ ሺህ ሰው ፊርማ አሰባስበው ነው ፌዴሬሽን ምክር ቤት ድረስ የሄዱት፡፡ እንግዲህ ይሄ ሁሉ ጫና፡ ወከባና ግድያ ባለበት በዚህ ወቅት ሃምሳ ሺህ ሰው ፊርማ ማሰባሰብ ከቻሉ ነጻነት አግኝተው ሁሉም ቦታ ቢንቀሳቀሱ የምን ያህል ሰው ፊርማ ማሰባሰብ እንደሚችሉ መገመቱ ቀላል ነው፡፡

ያለው እውነታ ይሄው ነው፡፡

**የወልቃይት ጠግዴ ሕዝብ መከራና ስቃይ**

አሁንም ከላይ የጠቀስኳቸውን የፕሮፌሰር ክላፐማንን ቋንቋ ልጠቀምና " ወልቃይትና ጠግዴ በኢትይኦጵያ ተሪክ በትግራይ ስር ሆነው አያውቁም"። ለመጀመርያ ግዜ በትግራይ ስር ፡ አለ - ህግ እና በማን አለብኝነት በትግራይ ስር በሀይል እንዲካተቱ የተደረገው በ1994 ነው።

ወልቃይት በ1994 ወደ ትግራይ እንድትካለል ከተደርገበት ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ የወልቃይት ሕዝብ እምቢታውንና እሮሮውን እንዳሰማ ነው። ሕዝቡ በግልጽ ቋንቋ እኛ ትግራዮች አይደለንም በማለት ተቅዎሞውን ቢያሰማም ፡ ሀገሪቱን የሚመራው ሕግ ሳይሆን ኃይል ስለሆነ ይህንን ጥያቄ በኃይል ለመጨፍለቅ ብዙ ዘግናኝ ነገሮች ተደርገዋል[9]። ታሪክን ያውቃሉ የተባሉ በርካታ አረጋውያን ተገድለዋል። እምቢታቸውን ያሰሙ አያሌጎም ልማሶች ተገድለዋል። የተደፈሩትን አካለ ስንኩል የሆኑትን እሱ ፈጣሪ ይቁጠራቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያዊነት የተባለው በዋሺንግተን ዲሲ የሚገኘው ሬድዩ ጣብያ በጁን 24, 2008 ያስተላለፈውን ዝግጅት ያድምጡ)። ነገር ግን ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ የጭካኔ በትር ቢወርድበትም አሁንም ሕዝቡ በግልጽ ቋንቋ " እኛ ትግሬዎች አይደለንም። መብታችን ይከበርልን ፡ የማንነት ጥያቄያችን ይመለስልን" በማለት ድምጹን እያሰማ ነው።

ይህን ጥያቄ ለማድበስበስና ለማጥፋት እንደ መፍትሄ እየወሰደ ያለው ፡ በርካታ የትግራይ ተወላጆችን ወልቃይትና ጠገዴ ላይ ማስፈር ነው። ይህ ሰፈራ አላማው ሁለት ነው። የመጀመርያው የሕዝቡን ቁጥር ሚዛን ለመጨመር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አብዛኞቹ ሰፋሪዎች ህወሀት ትግል ውስጥ በነበረበት ወቅት ይዋጉ የነበሩ ታጋዮች ስለሆኑ የአካባቢው ነባሩ ተወላጅ ለሚያነሳው ማናቸውም አይነት ጥያቄ እዛው በጠመንጃ ኃይል እንዲዳፈን ነው። ለዚህም ነው ሰፋሪዎች ሲሰፍሩ ሙሉ ትጥቅ የሚሰጣቸው። ከማንም በላይ ህወሀት እነዚህ ቦታዎች በግድና በሀይል የተያዙ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ወደፊት ሕዝበ ውሳኔ ቢካሄድ በሚል እሳቤ እሳሁን ብዙ ሕዝብ እያሰፈረ ነው።

የእነዚህ ቦታዎች ሁኔታ አሁን የሚደረገውን ለሚሰማ ፡ ለሚመለከት ሰው እጅግ ያሳዝናል ይደንቃልም። እንደሚታወቀው ወልቃይት የሱዳን ድንበር ነው። ተስፋፊዋ ሱዳን ከጥንት ጀምሮ የወልቃይትን ቦታ ለመውሰድ ያልጣረችበት ግዜ የለም። ከሱዳንና ከመሰል ወራሪዎች ጋር ለብዙ ዘመን ደም ተፋሰው ቦታውን በኢትዮጵያ ስር ሆኖ እንዲቆይ ያደረጉት ወልቃይቴዎች ናቸው፡ ፡ ዛሬ ግን ያለው ሁኔታ ያሳዝናል። ወልቃይቴዎች አባቶቻቸው ደማቸውን አፍሰው ባቆዩላቸው መሬት ላይ ባዕዳን ሆነዋል። በገዛ መንግስታቸው እነሱ እየተነቀሉ ሌላው ይተከላል። ቋንቋቸውንና ባህላቸውን እንኳን እንዳይጠቀሙ ተከልክለዋል። ያባቶቻቸው ደም በፈሰሰበት

---

[9] https://archive.org/details/scm-365062-atochalachewonwelkaittegede

አጥንታቸው በረገፈበት መሬታቸው ላይ ባዕዳን እንዲሆኑ እየተደረገ ነው።ዜግነታቸው ተረስቶ አሸባሪዎች እስከመባል ደርሰዋል።

ከተፈጥሮና ከእውነት ጋር ተጻራሪ የሆነ ነገር መውደቁ አይቀርም። በርግጠኝነት ይህ ጎጠኛ ስርዓት መውደቁ አይቀርም። ሌላው ቢቀር ግን የሚመለከት : ለግፉአን የሚፈርድ : አምላክ አለ። አንድ ቀን መፍረዱ አይቀርም። ታሪክ የሚያስተምረን ነገር አንድ ነው ፡; ይሄውም ምንግዜም -የተገፋ በደል የተፈጸምበት አካል ማሸነፉ አይቀርም። ግን እኔ በጣም የማዝነው በሁለት ነገር ነው። አንደኛው - እንደ ሕዝብ ይሄንን ያህል እየተገፋፋን ፡እየተጨካከንን መሄዳችን ያስደነግጣል። ያስፈራልም። ይሄን ያህል ቁርሾና ቂም ሕዝቡ ውስጥ ማሳደሩ የሚጠቅመው ማንን ይሆን? ስልጣን እኮ ትሾልካለች። ዛሬ ላይ የምንዘራው የክፋት ዘር ነገ አድጎ ከባድ መዘዝ እንድሚያመጣ እንዴት ማስተዋል ተሳነን? መማርና ፊደል መቁጠርስ- እንደ ሀናና ቀያፋ ያልተጻፈ ለማንበብና ንጹሃንን ለመወንጀል ይሆን? በ ጊዜ ለኩሉ ይላል መጽሓፍ። ለሁሉም ግዜ አለው።


ዋቤ መጻሕፍትና ሊንኮች

1. http://tigrigna.voanews.com/a/welkite-tsegedie-historical-perspective-by-dr-geladewos-araya-part-1-and-2/3253236.html
2. (https://play.google.com/books/reader?id=Y4WbCSAU7kQC&printsec=frontcover&output=reader&hl=en&pg=GBS.PA448)
3. https://archive.org/stream/routesinabyssini00cookrich#page/186/mode/2up/search/1
4. https://books.google.com/books?id=s05FAAAAYAAJ&printsec=frontcover&dq=james+bruce+volume+three&hl=en&sa=X&ved=0ahUKEwj90KO71ObLAhUMwGMKHa3SDHUQ6AEIHTAA#v=onepage&q=tigre&f=false
5. Tractatus tres historico-geographici (1634): A seventeenth century historical and geographical account of Tigray, Ethiopia (Aethiopistische Forschungen) 1634
6. https://books.google.com/books?id=kSgmwugWCGMC&pg=PA351&dq=tigray+map&hl=en&sa=X&ved=0ahUKEwiJ8YKTg-DLAhVN42MKHbyiA9Y4ChDoAQhKMAQ#v=onepage&q=tigray%20map&f=false
7. Christopher Clapham: Transformation and continuity in revolutionary Ethiopia (Cambridge: Cambridge university press 1988 pp 259
8. The World through Maps: A History of Cartography : John R Short
9. https://archive.org/details/liberaxumae00pari ( the Book of Axum part one)
10. Library of Congress የኢትዮጵያ ካርታ 1955 ዓ.ም (በ1963 እ.ኤ.አ ወይም)
https://www.loc.gov/resource/g8330.ct002884/

11. (https://www.loc.gov/resource/frdcstdy.ethiopiacountrys00ofca_0/?sp=26)
የኢትዮጵያ ካርታ 1966 ዓ.ም (በ1974 እ.ኤ.አ ወይም) Library of Congress

12. Library of Congress የኢትዮጵያ ካርታ 1979-81 ዓ.ም
https://www.loc.gov/resource/frdcstdy.ethiopiacountrys00ofca_0/?sp=27

13. በ1928 ዓ.ም ( 1933 እ.ኤ.አ) ጣልያን የሰራው የኢትዮጵያ ካርታ
http://www.igmi.org/ancient/immagine.php?cod=13698

14. በ1928 ዓ.ም ( 1933 እ.ኤ.አ) ጣልያን የሰራው የኢትዮጵያ ካርታ
http://www.igmi.org/ancient/immagine.php?cod=14557

15. https://www.loc.gov/search/?in=&q=ethiopia&new=true
( CIA maps 1961 E.C and 1969 G.C)